# <u>እንጻፍ ከተባለ</u>

ኢያሱ ዓለማየሁ

*" የማይጽፍ ደብተራ፤ከንፍ የሊለው አሞራ"*

ለደብተራነቱ ባልበቃም ደብተራዎችን የማወቅ ዕድል ስለነበረኝና የደብተራውን ደብተራ ጺጋዬ ገብረመድህንን ጓድ የማለቱን ዕድል አግኝቼም ስለነበር አልፎ አልፎ--ብዙውን ጊዜ "አልበዝቶም ለማለት"--ያው አጅሪዎችን የሚያንጨረጭር ጽሁፍ መጻፌ አልቀረም ። ይህም በዚያው መንፈስ ይታይልኝ። ቁራ መቸም ባይነጣም፤ ማለትም የሚመለከታቸው መቸም የሚታረሙ ባይሆኑም ድምጽ ማሰማቱ ደግሞ ግዴታ ነው። በተለይ ውድ ሕይወታቸውን ለሀገር በሰጡት ላይ ጺያፍ ዘለፋና ዘመቻ ሲካሂድ ።

ባለፈው ኢሕአፓና ታሪኩ ብዬ በመጻፌ የተነኩ የሚጠበቀውን ውርጅብኝ አውርደውብኛል። ዛሬ ለክስ የተዳረጉ የሀገር ቤት መጽሔቶች ደግሞ አትመውልኝም ነበር ። ወያኔም በድረ ገጹ አማካይነት ስም ጠቅሶ በሉት በሉት ብሎ ጩኸት አሰምቷል ። ወያኔ የኢትዮጵያን ታሪክ ዓመትን ወደ መቶ ዓመት አውርዶና ሀገሪቷን የሌሎች ቅኝ ገዢ  አድርጎ፤ ሕዝብ በአንድነት ሊኖር አይፈልግም/አይችልምም በሚል የጥፋት ተልዕኮውን ከቤተመንግስት እንዳደረሰው ሁሉ ኢሕአፓን በጦር ከማጥቃቱ አልፎ ለስልጣን ከበቃ ጊዜ ጀምሮ የኢሕአፓን ታሪክ ለማበላሸት በስፋት ተንቀሳቅሷል። ተራራ ያንቀጠቀጠ ትውልድና እፎይታ የሚባለውንም መጽሄት ኋላ ከወያኔ ይልቅ የሻዕቢያ ቅጥረኛ መሆኑ በተጋለጠ ግለሰብ አማካይነት የድርጅቱን ታሪክ አበላሽቶ ሊያቀርብ ሞከረ። በቀይ ሽብር ሰማዕትም ሊነግድ ሞክሮ በኢሕአፓና ሊሎችም ተቃውሞ ከሸፈበት ። ሳይውል ሳያድር የወንጀሉን ሸክም ከደርግ ጫንቃ አንስቶ ወደ ኢሕአፓ አዛወረው። ለዚህም ተባባሪ የሚሆኑት በጽሁፍና በፕሮፕጋንዳ ደረጃ አሰማራ። መጽሐፍት ተጻፉ። ተጠቂውና ሰለባ የሆነው ኢሕአፓ አስፈጂና ገዳይ ተብሎ ተወነጀለ ። ዘመቻው ቅጥና ለከት አጥቶ አረመኔ ነፍሰ ገዳዮች (መንግስቱ፤ ፍቅረሥላሴ፤ ሌሎች የሚቀጥሉም ይኖራሉ) ወንጀላቸውን እየካዱና ኢሕአፓን እየወነጀሉ መጽሃፍ እንዲያትሙና እንዲያሰራጩ ዕድል ተሰጣቸው። መጽሐፍ መጻፉ በራሱ ብቻ ፋይዳ እንደሊለው በዚሁም ሊታይ ችሏል። በዚሁ መንፈስ ወያኔ ያዘጋጃቸው ወይም በስተርጅና ዘረኝነት የተጠናወታቸው ዛሬም ኢሕአፓና አመራሩን የሚያወግዝና ድርጅትና ህዝብን የጎዱትን ሁሉ የሚያወድስ መጽሐፍ ለማቅረብ ደፋ ቀና እያሉ ናቸው ።

ሊበሷት የፈለጓትን አሞራ ጅግራ ይሏታል የተባለውን በግልባጩ እንረዳውና ወያኔ ጠላት ያላቸውን ሁሉ ታሪክ በሀሰት ማቅረቡ የትግል ስልቱ አካል ሆኖ ቆይቷል። ኢትዮጵያን ለመገነጣጠል የተነሱ ሁሉ ያጀቡት የወያኔ ቅጥፈት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር አልነበረችም ወይም መቶ ዓመት ብቻ ነው ታሪኳ (የሻዕቢያው መሪ በቅርቡ “ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የመጣችው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ” ማለቱ ይታወሳል) ማለት ለግንጠላ ትግላቸው አመቺ ነውና የሀሰት ታሪክ ሲፈታትሉ ፤ ሲያሰራጩና ኢትዮጵያን በሚጠሉ ባዕዳንም ዘንድ ሲስተጋቡ ቆይተዋል ። ኢሕአፓ የወያኔን የግንጠላ መርህ ግብር በ 1967 ሲወጣ ጀምሮ የተቃወመው በመሆኑ አባ ኢትዮጵያ--አማራ ትምክህተኛ ተብሎ በወያኔና በሊሎችም ሲወገዝ ባጅቷል። በአሲምባ ያ ሁሉ የኢሕአፓ ታጋይ ውልደቱ ከትግራይና ኤርትራ ሆኖ ባለበት ሁኔታ ወያኔ ድርጅቱን የአማራ ትምክህተኛ ብሎ ሊሰይም አልቀፈፈውም ። ወያኔ ውሸትና ጠላን (ሰዋን) ሽምጥጥ ነው በሚል ያምናልና እስከዛሬም ጠላት ባለው ሁሉ ላይ (ከሀገር እስከ ድርጅትና ግለሰብ ) የውሸት ናዳን ማውረድ የሚያምንበትና የሚገለገልበት ነው ። ስለዚህም የሚፈራውን ኢሕአፓን ለማስጠላትና ለማጥቃት ሲነሳ ወያኔ አልለውም የሚለው ውሸት አልነበረም፤ የለምም። ስብሓት ነጋ

ሶማሊያ ወደ ኢትዮጵያ ስትዘምት ከደርግ ጎን ሆነን ለመሰለፍ ጠይቀን ነበር ያለውን ዓይን አውጣ ውሸት ያስታውሷል! ኢሕአፓን እስከጠሉና እስከተቃወሙ ድረስ በወያኔ (ቢቀፉትም) ይታቀፋሉ፤ ይበረታታሉ፤ ይደገፋሉ ። በመሆኑም በኢሕአፓ ላይ ታሪክ ነን ብለው የተጻፉ ተረት ተረቶች ሁሉ ድርጅቱን እስከ ዘለፉና እስካሳጡ ድረስ ወያኔ ገበያ ሰጥቷቸዋል። የወያኔ የአሉባልታም ፋብሪካ ሙብራትና ውሃ አጥሮት የተዘጋበት ቀን የለም ። ኢሕአፓን ሲያወግዙ እግረ መንገዳቸውን ደርግን ቢያወድሱ ወያኔ ይህስ በዛ ሲል አልተደመጠም፤ ሊደመጥም አይጠበቅም ። ለዚህም ነው አስከሬንን በጥይት ዋጋ የቀየረውን አገዛዝ ከመሩት መካከል አንዱ (ፍቅረስላሴ) ሀገሪቷን ከጥፋት አዳንን፤ ምስጋና ይገባናል ሲል (ጸረ ህዝብ ወንጀልህን ዳግም ካድክ በማለትና በማሰር ፈንታ) አጀሃ (አይዞህ) የሚለው ።

በደፈናው መጽሃፍ ስለወጣ እሰየው የሚባል አይደለም ። የሂትለርም ማይን ካምፕፍ (የኔ ትግል ማለት ነው) የመንግስቱም ትግላችን መጽሐፍት ናቸው። የታሪክ መጽሀፍ ለመሆን ግን የጋራ ቅርስንና እውነታን የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። የግል ታሪክ ከሆነ ደግሞ ይህ በግልጽ መቀመጥ ያለበት ነው። ለምሳሌ በካናዳ ነዋሪ የሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ የግሌ ታሪክ ብሎ የጻፈው ውሸት ተብሎ ከመጋለጡ ሌላ መጽሃፉንም የጻፈችለት ሌላ የካናዳ ዜጋ ፈረንጅ መሆኗ ተጋልጦ ዜጎችን አሳፍሯል-- የግል ታሪክ ብሎ መዋሸት አይቻልም ለማለት ነው። ታሪክ የሚጻፍበት ቀለም ውሸትና ቁርሾ ከሆነ ከተመከሮ ለመገንዘብ እንደሚቻለው መጨረሻው ከቶም አያምርም። ወደ ትችት ጋባዥነት ያመራል -- መጻፍ ያቃተው ደራሲ ታሪክ ተራኪ ሆነም ያሰኛል። አልፎም ያለፈውንና የሆነውን የሚቀይሩ ታሪክ ጸሃፊዎች ብቻ ናቸው አስብሎ ለስላቅ ይዳርጋል ። በታሪክ እያንዳንዱ ንጉስ የራሱን የብዕር ቅጥረኞች አሰማርቶ ታሪክን ባፈተተው ያጽፋል ። አጼ ሀይለ ስላሴ ለምሳሌ በአጼ ቴዎድሮስና ልጅ ኢያሱ ላይ የሚያጥላላ ታሪክ አጽፈው ነበር ---- የራሳቸውንም ዝና ይበልጥ ለማጋነን ማለት ነው ። ኢትዮጵያ ራሷ ልብወለድ ነች ብለው መጽሐፍ የጻፉም ነበሩ። ታሪክ በአብዛኛው በሆነ ነገር ላይ ውሸት ትረካ ሊሆን አይገባውም ። ወያኔ ለምሳሌ ስለድርጅቱም ሆነ ስለ ግለሰብ መሪዎቹ ልብ ወለድን ሀቅ ብሎ ለማቅረብ ሞክሮ የነበሩ አጋልጠውታል (በመለስና ስዩም መስፍን ታሪክ ተብዪ መጽሃፍት ላይ የቀረበውን ትችት ሁሉ ያጢኗል)። በበኩሌ ጊዜ ሰጥቶኝ ገብሩ አስራት የተባለው የወያኔ የቀድሞ መሪ ጻፈው የተባለውን መጽሐፍ ገና አላነበብኩትም ። ቀደም ብሎ የሰዪውን አንገቤ ከጻፈው የደበቀውን (የወያኔን ገበና የእኔ ብሎ ያልጻፈውን) ከመታዘብ ሌላ ፍሬ አላገኘሁበትም ። ከመለስ ተጣላን ያሉ የወያኔ መሪዎችና የወንጀሉ ተባባሪዎች፤ አንድም ሆድ ይፍጀው ዝምታን የመረጡ ሲሆን ከጻፉም የፈረደበትን ኢሕአፓን መስደብና ወንጀላቸውን መደበቅ ብቻ ነው ልማዳቸው። ማለትም ከወያኔነት አልተጣሉም፤ ለፈጸሙት ግፍ አልተጸጸቱም ማለት ነው ። የለየለትና ያከረረ የከረረ ወያኔ ሆኖ የቀየውና አሁንም አረና ነኝ፤ ተቃዋሚ ነኝ ቢልም ልቡ ከወያኔ ጋር ነው ብለው ወዳጆቹ እንኳን የሚከሱት ገብሩ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ አብሮ ከነመለስ ጋር ስላሰራጨው የጠባብ ብሔርተኛነትና የግንጠላ መርዝ ሳይደብቅ ካወሳ፤ ራሱ በነበረበት የቤተ እስራኤሎች ንግድ ላይ የወያኔን ሚና ካጋለጠ፤ የትግራይ ገዢና የወያኔ ከፍተኛ አመራር በነበረ ጊዜ በትግራይ ስላጠፏቸው እነ ጸጋዬ፤ ይስሓቅ፤ አምሐ፤ በለጠ ወዘተ... የት እንደደረሱ ከገለጠ፤ በመቀሌ እስር ቤት ከ 4000 ያላነሱ እስረኞቹን (ብዙዎቹ ሻዕቢያን ተቃወማችሁ ተብለው) ሁኔታ ገልጾ በበቂ ከጻፈ፤ የወያኔን መሰረታዊ ጸረ ኢትዮጵያዊነት ካጋለጠ (ሁሉንም የወያኔ ግፍ ገበና -የራሱም ነውና ያጋልጣል ብለን ባንጠብቅም--ያኔ የረባ መጽሐፍ ብለን ገንዘብም ጊዜም ልናጠፋበት እንችላለን ። ስውር ደራሲዎቻቸው መጽሐፋቸው ነው ብለው ለክፍያ ያጠናቀሩትን ማለት ነው ። ሕዝብን የፈጁና ያስፈጁ ወይም በጸረ ሕዝብ ወንጀል የተሳተፉትን መድረክ እየሰጡ፤ መጽሐፍ እያተሙና እያሰራጩ በሕዝብ ደም ላይ የሚቀልዱትም ተጠያቂነታቸው ሳይጠቅስ የሚታለፍ አይደለም ።

እንጻፍ ብለን ከተነሳን ሀቁን መሆን አለበት። ሀቅ ደግሞ የሚነገርበትና የሚጻፍበት ጊዜ አለው። በለሆሳስም ተጠቅሶ የሚታለፍ ሊሆን ይችላል/ይገባልም ። በህዝብ ታሪክ ላይ ጥላሸት የሚቀቡ ክስተቶች አንዳንዴ ለመጪው ትውልድ ጆሮ ባይገቡ ይመረጣል ሊባል ይችላል። አከራካሪ ነው ። ለማንኛውም ግን ታሪክ ሀቅን አቅራቢ መሆን አለበት ። በስማ በለውና በነበር ደረጃ ታሪክ አይጻፍም፤ ከተሞከረም ውጤቱ አሳፋሪም ሊሆን ይችላል ። የግለሰብ ምኞት፤ ሰምቻለሁ ሲባል ዓይነት ታሪክ ሳይሆኑ የአሉባልታ የቤት ልጆች ናቸው። ኢሕአፓ እስከዛሬ በትግል መቀጠሉን ዓይናቸውን ጨፍነው የሚክዱ አንዳሉ ሰሞኑን በወያኔ ድረ ገጽ ላይ ኢሕአፓ በ1972 ፈራረሰ የሚለው ጽሁፍ ብቻ ሳይሆን በ1972ም ሆነ ከዚያ ብዙ ሳይቆዩ የከዱትም የሚደጋግሙት ነው ። እኛ ድርጅቱን ስንተው ድርጅቱ አበቃለት ዓይነት ግብዝነት። ሀቁ ይነገር ከተባለ የኢሕአፓ ሠራዊት ይህ ነው የሚባል ረጅም ትግል ያካሄደው የብተና አደጋ ደርሶበት ታሪክ ጸሃፊ ነን ወይም እንሆናለን የሚሉት ሁሉ ጥለውት ወደየፊናቸው ከተጓዙ በኋላ ነው። ወያኔ ለስልጣን በቅቶ ባለበትም እንኳን እነ ጓድ መስከረም፤ ጃብር (የአመራር አባል)፤ ግርማ ጎልጃና ሌሎቹም በቋራ ወያኔን ታግለው መስዋዕትነትን ተቀብለዋል። ከጠፉ ስንት ዓመቱ የሚባለውን ድርጅት ወክለው እነ ኃይም፤ ለማ፤ ጸጋዬ፤ ወንዱ ሲራክ ደስታ፤ ኢዮብ፤ ሞት ባይኖርና ስንቱ ወርቅ ጓዶቻችን ተሰውተዋል ወይም ደብዛቸው በወያኔ እጅ ጠፍቷል ። በድርጅቱ ነበርን ብለው ስለ ኢሕአፓ የጻፉት (ከአንዱ በስተቀር) ሁሉም ድርጅቱን ከ1969 እስከ 1972 ባለው ጊዜ ጥለው የሄዱ ናቸው ። የግል ስሜታቸውን የፖለቲካ መጽሃፍ ለማድረግ ከጣሩት ውስጥ አንዱ የድርጅታችንን ብረት ይዞ ወደ ጅብህ ሲከዳ ሌላዋ ደግሞ በአንጃነት ተሰልፋ በዚያው የነጎደች ናት። እነዚህም ሆኑ አመራር ነበርን የሚሉት ከዚያ ከ 1972 ወዲህ ምንም የፖለቲካ እንቃስቃሴ ያላደረጉ፤ ከወያኔ ሰምረው ለወያኔ የሰሩና አዲስ አበባ የሚመላለሱ ናቸው ። እንጻፍ ካልንማ ዝርዝሩ ለነዚህ ሁሉ አያመችም ። አሉታዊ ሚናቸውን ከነ አሳፋሪ ዝርዝሩ ልንገባበት ነው፤ አሁን ደግሞ ካለው ባለነፍጥ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ወዳጅነት ልንተች ነው ።

ወያኔም ሆነ በኢሕአፓ ላይ እየዘመቱ ያሉት ጥርቅሞች በሞላ ሀቅን ወደ ኋላ አጉብጠው በድርጅቱ ላይ የተነሱት የአንጃ ቡድኖች በሞላ ትክክል ነበር ይላሉ ። ድርጅቱ ሲቃወሙት ይገድላል፤ አንጃ ብሎ ያጠቃልም በሚል ክስ ይደረድራሉ ። በተለይ በርካታ አባሎቹን የረሸነው ወያኔ፤ እርቅ ብሎ ጠርቶ የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት መሪዎችን በተኙበት በአለት ድንጋይና በስለት የፈጀው (የአይጋ ሕዝብ ጥይት ሰምቶ ምንድነው እንዳይል) አረመኔ ቡድን ኢሕአፓን ተቃዋሚን ገደለ ሊል አይችልም:: ድርጅቱ እንዲያውም የሚከሰሰው በሠራዊቱ ልቅ ዲሞክራሲን በማስፈን ነው ሲባል ተውቅሶበታል። ድርጅቱ የተቃወሙትን የሚገድል ከነበር ዛሬ በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካ ያሉ የያኔ ተቃዋሚዎቹን ዝም ብሎ ባልተዋቸው ነበር፤ ማንም ሰራዊቱን መልቀቅ የሚፈልግ መልቀቅ ይችላል ብሎ የአቅሙን መሸኛ ገንዘብ እየሰጠ ባልሰደደ ነበር። እንጻፍ ካልን ደግሞ ከአንጃ ቁጥር 1 እስከ አንጃ ቁጥር 3 (በመሀሉ በታኞችን ጨምሮ) በድርጅቱ ላይ ያደረሱትን ከፍተኛ ጉዳትና የማይጠበቅ ሻጥር መዘርዘር ይኖርብናል። ኢሕአፓ የተቃውሙትን አንጃ ብሎ ወይም ሊሎች እንደሚቀናቸው ደርግ ወይም ወያኔ ብሎ አይወነጅልም። አንጃ ለማለት ግን የሚገፋው ተቃወምን የሚሉት የድርጅቱን ህግና ደምብ፤ ስነ ስርአት ጥሰው በቡድነኝነትና በአፍራሽነት ሲሰማሩ ነው። ለምሳሌ የአንጃ ቁጥር አንድ ሁለት መሪዎች ከደርግ ጋር ተባብረን እንስራ ያሉት ሀሳባቸው ወደ አባላት ወርዶላቸው (ያውም በዚያ ቀውጢ ጊዜ) ተቀባይነትን ሲያጣ ወደ ህገ ወጥ ተግባሮች የተሸጋገሩ በመሆኑ አንጃ መባላቸው ተገቢ ነበር። ደርግ ለጀመረው አፈናና ጥቃት በመካላከል ደረጃ የተወሰደውን እርምጃም መቃወማቸው ከነበራቸው ደርግ ዲሞክራሲያዊ ነው እንተባባረው ከሚለው አቋማቸው ጋር የተያያዘ በመሆኑ የሚጠበቅ ነበር ማለት እንችላለን :: ልዩነቱ በትግል ስልት ሳይሆን ደርግ ማነው? ጸረ ህዝብ አምባገነን ወይስ ዲሞክራሲያዊ በሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ነበር ። ይህ አንጃ በጓዶችና በድርጅቱ ላይ ያደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት የነበሩትና ሰለባ የሆኑት ያውቁታል፤ በአንጃ ተጋልጠው ያለቁት ጓዶቻችን ደግሞ የደም ምስክርነት ሰጥተዋል ።

አንጃ ቁጥር ሁለትም በአሲምባ አንጃ ሊባሉ የበቁት ባቀረቡት ሀሳብ ወይም ተቃውሞ ሳይሆን ህግና ደምብን ጥሰው ውስጥ ለውስጥ ስለተደራጁና በቡድን ሆነው በህጋዊ አመራሩ ላይ እርምጃ ሊወስዱ ስለተነሱ ነው። በአባላት ተጋልጠው የተያዙትም የቡድኑ/አንጃው አባላት ችሎታ ያላቸው ጠበቃዎች ቆመውላቸው በትሪቡን ፊት ቀርበው ቅጣት የተፈረደባቸውም የተለቀቁም ነበሩ ። በወቅቱ ሁሉም አባላት ተወያይተውበትና ተስማምተው ባጸደቁት የሰራዊት ሕግ መሰረት በሰራዊቱ ውስጥ አንጃ መፍጠር በሞት ያስቀጣ ነበር። አንጃ ቁጥር ሶስት የተከሰተው ደግሞ ለወያኔ አፈዳቪት ፈርመን ወይም ህገ ወያኔን ተቀብለን፤ ብረት አናነሳብህም ብለን ምለን እስረኞችቻንን ፈታ አልፈታ ገብተን በስሩ እንሰለፍ ብሎ የተነሳ ነበር ። ምንም እንኳን ይህ የጥቂቶች አቋም ቢሆንም በጠየቁት መሰረት የጻፉት ወረቀት ወደ አባላት ወርዶ (ይህ ሰነድ በድርጅቱም በአባላትም እጅ አለ) አባላት ውድቅ ሲያደርጉት የሀሳቡ አቅራቢዎች ውስጥ ለውስጥ ከድርጅቱ ህግ በተጻረረ መደራጀት ጀምረው፤ ድርጅቱን ሊቆጣጠሩና ወደ ወያኔ ሊከንፉ ባላቸው ፍላጎት ልዩ ጉባዔ ይጠራልን ብለውና ተጠርቶላቸው ብዙሃን መሆን ሲያቅታቸው ጉባኤውን በውድቅትና በጠዋት ረግጠው ወጥተው፤ የድርጅቱን ስም ሊቀሙና ለጠላት ጠቃሚ ስራ ሊያከናውኑ የሞከሩ ናቸው ። ሌሎች ጸያፍ ድርጊቶቻቸውን በዚህ ማንሳቱ አስፈላጊ ባይሆንም እንጻፍ ብለን ስንነሳ በዝምታ የማንልፋቸው አይሆኑም ። ከወያኔ የጸጥታ ሀላፊ ጋር በምስጢር ያደረጉትንም ግንኙነት በዝርዝር የምናቀርበው ይሆናል። በአጭሩ ተቃዋሚ ሀሳቦችን ኢሕአፓ አስተናግዷል፤ በድርጅቱ ውስጥ ህግን ጥሶ ቡድን ምስረታን ግን በቸልታ አላየም ። ይህም በድርጅቱም በሰራዊቱም ህግ ቁልጭ ብሎ የተቀመጠ ስለሆነ ቡድንና አንጃ መስራቾች ቅጣቱ ምን እንደሆነ አስቀድመው የሚያውቁትና ህግ ብለውም ራሳቸው ያጸደቁት ነው ።

ይህ ሁሉ አባይን በጭልፋ እንጂ ዝርዝር አይደለም። ምናልባትም ኢሕአፓ ያጋጠሙትን ድርጅታዊ ችግሮች ለብቻው አስፋፍቶ ማቅረቡ ለሌሎች ድርጅቶችም ይጠቅም ይሆናል--እንዴት እንደተቋቋማቸውም ተመክሮ ነው። ቀደም ሲል ኢሕአፓ ተሳሳትኩ ያለበትን ደግሞ ደጋግሞ ይፋ አድርጓል ። ፋሺስቱን ደርግ መታገሌ ስህተት ነበር ማለት አለበት ካሉ ግን አዎንታዊ መልስ የሚያገኙት ከአንጃዎችና መሰሎቻቸው ይሆናል እንጂ ከኢሕአፓ አያገኙትም--መቸም ቢሆን መቼ ! የከተማው ግፍጫ ብዙ ጉዳት አላደረሰምን? አዎ አድርሷል። ከነበረው ሁኔታ ጋር ተያይዞ ሲታይ የመከላከል እርምጃው መገፋቱ ስህተት ሊባል ቢችልም ምናልባትም ሊታለፍ የማይችል የትግል ሂደት ነበር ማለትም ይቻላል ። ኢሕአፓ ወጣቱን አስጨረሰ ይላሉ እነ ወያኔ ሳይቀሩ--ራሳቸው የተሳተፉበት ቀይ ሽብር የገደሉብን አባላት እያሉ እየዘከሩ ። ስንቱን የትግራይ ወጣት ወደ ናቅፋ ልከው ለጠመንጃ ልዋጭ አድርገው እንዳላስፈጁ ሁሉ! ስንቱን ለአቅመ አዳም-- ሒዋን ያልደረሱ ወጣቶችን አስጨርሰው ለድል እንዳልበቁ ሁሉ! በኢሕአፓ ስር ተሰልፈው ሕይወታቸውን ለሀገራቸው የሰጡት ጀግኖች የተሳሳተ መስመርና ውሳኔ ሰለባ ሳይሆኑ የሚዘከሩና አርአያ የሆኑ ጀግኖች ናቸው ። ትግላቸውን ለማቅለልና የፍጅቱን አራማጅ ደርግን ሳይሆን ሰለባውን ኢሕአፓና ሕዝብን ለመውቀስና ለመክሰስ የሚደከሙት ሁሉ ታሪክ ውዳቂ ትላቸዋለች ። ዛሮች የእኛው ጠማማ እንዲሉ በሰማእትና ድርጅቱ ላይ ጸያፍ ዘመቻን የሚያካሂዱና እንደ ውሻ ወደ እንትናቸው የሚመለሱ ከራሱ ከድርጅቱ ውስጥ መውጣታቸውም የሚያስገርም አይደለም። ሐሚተኛ ነው ከዳተኛ ይላል የሀገራችን ሰው ። ድርጅት በአንድ በኩሉ አጸደ ሕጻናት መሆኑ ይታወቃል ። በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ የሚለው ስሚ አግኝቶ ደጋፊው ሲበዛ ወደ ጎርፉ ዘው ብለው አባል ነን የሚሉም የድል ተቀራማቾች ለመሆን የሚቋምጡም ይኖራሉ ። በታሪክ አጋጣሚ ደግሞ አንዳንድ ግለሰቦች ችሎታና ጽናቱ ሳይኖራቸው ወደ አመራር ቦታም ሊደርሱ ይችላሉ ። ይህ ሁሉ በድርጅቱ ሂደት ላይ የማይናቅ ተጽዕኖ አለው ። ይህንን በዝርዝሩ የምንጽፈውና ከዚህ አንጻርም ብዙዎች በሚገባ የማያውቁትን ማሳወቅ ግዴታችን ይሆናል። ድርጅት ጥቃት ሲደርስበት ወይም ያሰበው ግብ ሳይሳካለት በቀቢጸ ተስፋ ድርጅቱን ለቀው የሚወጡ፤ድርጅቱን ጥፋተኛ ብለው የሚኮንኑ፡ ለታገሉት ጠላት የሚሰግዱ፤ እምነት ርዕዮታቸውን

የሚሽሩና ማረን ማረን ባዮች በርካታ ናቸው። በሌሎችም ታይቷል፤ በእኛም በኢሕአፓም በቅንጅትም ታይቷል ፡፡ በዚህ ቀውጢ ጊዜ ግን እምነትን ጠብቆና ሞት አይፈሬ ሆኖ ድርጅትን ማስቀጠል ግን የሚከበር ጀግንነት ነው ። ኢሕአፓ በ1972 አልፈረሰም--በ2004 ዓ.ም. 42ኛ ዓመቱን አከብሯል ። ሐፍረት ለከሀዲዎች ! ይብላኝ ለአንጃዎች !

ድርጅቱ ፈርሷል ፤ የለም የሚሉት ክፍሎች በጠፉ ድርጅት ላይ ብዙ ጊዜ ሲያጠፉ እየታዘብን ነው ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወያኔ ጫንቃው እየከበደው፤ እየቀፈፈው ነውና ግፍ የበዛበት ሕዝብ ሆ ብሎ ሊነሳብኝ ይችላል ብሎ ይፈራል ። ለዚህም አመጽ፤ ለህቡዕ አሰራርና በጸረ ህዝቦች ላይ እርምጃ መውሰድን በተመለከተ የኢሕአፓ ተመክሮ ትምህርታዊ በመሆኑ ወያኔ ይህን ተመክሮ ማራከስ ዋና ተልዕኮው ሆኗል። አብዮት አንፈልግም የሚለው ቀረርቶም የዚሁ ነጸብራቅ ነው። አባል ነበርን ብለው ድርጅቱ ላይ የሚዘምቱትን ሀይ ሀይ እንዳለው ሁሉ የዛሬ 34 አመት አመራር አባል ነበርን የሚሉንም አዘጋጅቷል--የኢሕአፓን የገጠርም ሆነ የከተማ የትግል ተመክሮ ጭፍን ስህተት ነው ለማለት፤ በሕይወት ያሉና የቆዩትንም አመራር በሆነ ባልሆነው፤ በነሩበትና በሌሉበትም ሁሉ ለመወንጀልና ስም ለማጥፋት ። ድርጅታቸውን ከድተውና በሰቡብ አስባቡ ጥለው የፈረጠጡና የሄዱ ለወያኔ አድረው ዓመታት ካሳለፉ ወዲያ በድንገት ተገልብጠው የረሱትን፤ የጎዱትንና የማያውቁትን ኢሕአፓ የለም፤ ፈርሷል በሚል ዋና ወሬ አናፋሽ ሆነው ተሰልፍዋል ። ያልታወቀና አሰባሳቢ ያልነበረን ዘር ቆጠራንም ሊያሰፍኑ ተነስተዋል ። የኢትዮጵያ ተማሪ እንቅስቃሴ ልዩና ጠንካራ ያደረገው በጎሳ በብሔረሰብ አለመከፋፈሉና በኢትዮጵያዊነት መደራጀቱና መሰለፉ ሲሆን ኢሕአፓም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ድርጅት እንጂ ዘር ቆጥሮ የተደራጀ አልነበረም ። ወያኔ እነዚህ መሰረታዊ ሀቆች እንዲታወሱም አይፈልግም ። በየካቲት አብዮት ሁሉም በኢትዮጵያዊነትና በጋራ የፖለቲካ ጥያቄዎች ዙሪያ ሲደራጅ ጠባቦቹ ግን ትግራይ ወዘተ ብለው በጎጥ መደራጀታቸውን ደግሞ መደበቅ የሚቻል ጉዳይ አይደለም ። በአጠቃላይ ያለን ነገር የለም ማለት ራስን ማታለያ የሰጎን ፖለቲካ ነው ።

ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲከኞች-ዛሬ የፖለቲካውን መድረክ ያጨናነቁት-- የፖለቲካ ትግልን እንደ እግር ኳስ ግጥሚያ ማየት ይቀናቸዋል ። ማን አሸነፈ? ስንት ጎል ማን አገባ፡ ለስልጣን በቃ? በሚል ግልብ ይዘቱ ይገምታሉ፤ ይደመድማሉም ። በቅርቡ በአንድንድ ድረገፅ እየተነበበ ያለውም የሚያመልከተው ይህንኑ የተሳሳተ አስተያየት ነው። ጥያቄው ግን ጠለቅ ያለ ነው ። ማንኛውም የፖለቲካ ትግል የስልጣን ጥያቄ ነው ቢባልም አንድ ድርጅት ወይም ትግል ስልጣን ካልያዘ ተሸነፈ ብሎ በፍጹም ደረጃ መደምደም ትክክል አይደለም። በትግሉ ሂደት በርካታ ድሎችን አግንቶ የመጪውን ፖለቲካ ሁኔታ ይቃኛል፤ ለውጥም ያስመዘግባል ። የኢሕአፓና የዚያ ትውልድ ትግል በሀገሪቷ የፖለቲካ ገጽታ ላይ ትላልቅ ማህተምን አስፍሯል። በፖለቲካ ድርጅት መልክ መሰባሰብ፤ ሁሉን አቀፍ ትግል ማካሄድ፤ የህዝብን መሰረታዊ ጥያቂዎች ቀዳሚ ማድረግና ንጥር አድርጎም ማውጣት፤ የተደራጀ የትጥቅ ትግል ተመክሮ፤ የሴቶች ተሳትፎ፤ ሁለገብ ትግል፤ የአርበኞች ቅርስ ተሃድሶና ሌላም የሕዝብ የትግል ቅርስ ሆኖ በጭፍን ሊገዙት በተነሱት ላይ የእምቢታን ከበሮ ያስደልቅባቸዋል ፡፡ ወያኔም በፈለገው መሰረት ሊገዛ ያልቻለው ፤ ገንጣይ አይደለሁም ኢሕአዴግ ነኝ ብሎ ለመታጠፍ የተገደደውና በግብሩ ባይሆንም የማይፈልጋቸውን መርሆዎች ለይስሙላም መቀበል የተገደደው በአቋምና ርዕዮት ደረጃ ተቸንፎ ነው ። ኢሕአፓ ለስልጣን የሚበቃው ሕዝብ የሙብቱ ባለቤትና ባለድል ሆኖ ኢሕአፓን ሲመርጠው ነው። ሕዝብ ባለድል እስካልሆነ ድረስ ኢሕአፓ ለስልጣን ሊበቃ አይችልም። ኢሕአፓ ለስልጣን ባይበቃም ተሸንፎ ክምድር ገጽ አልጠፋም--ትግሉን እስከቀጠለ ድረስ የተዳፈነ እሳት ሁሌም እሳት እንደሆነው ሁሉ ወያኔን የሚያስጨንቅ ሀይል ሆኖ ይገኛል ። ትግሉን ጥሎ ሲተው፤ ቃል ኪዳኑን ሲያፈርስና ይባስ ብሎ አንዳንዶች እንዳደረጉት ለወያኔ ሲሰግድ ያኔ እውነትም ተሸነፈ ማለት ይቻላል ፡፡ የሽንፈት ምልክቶች ግን ቃል ኪዳናቸውን ያፈረሱትና ድርጅቱን የካዱት አንጃዎችና መሰሎቻቸው ናቸው ። ለማንኛውም ኢሕአፓ ተሸነፈ አልተሸነፈ

ጉንጭ አልፋ ክርክር ነው እንበልና የአሁኑ ትውልድ ዋና ግዴታ በራሱ ጊዜና ዘመን መታገል ነው ። በኢሕአፓ ላይ ማላዘኑ--ያውም ሀሰት ታሪክን መሰረት አድርጎ-- ፍሪ ቢስ ነው ። ባለፈው ትውልድ ላይ የዛሬውን ግዴታ መለጋቱም ስህተት ነው--ተክቶ ግዳጅን መረከብ እንጂ ። ያ ትውልድ በመሰለውና ባመነበት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ--ለጎጥና ለግል ጥቅም ሳይሆን--ታግሎ ተሰውቶ የአርበኝነት፤ የጀግንነት ታሪክ ጽፏል፡፡ ከአሁኑ ትውልድ የሚጠበቀው ድሮ ስህተት ተሰራ ብሎ በጉንጭ አልፋ ክርክር ዙሪያ ተግባር አልባነትን መደበቅ ሳይሆን ሚዳውም ያው ፈረሱም ይሀው ብሎ ተነስቶ የትግል ታሪክን ማደስ እንጂ በጎሳ እየተለያየና ትግልንም እየፈራ ዋይ ዋይ ሀገሬ ማለት አይደለም ። ነገሮችን በተከሰቱበት ሁኔታ የጊዜ ክልል ማየቱ አስፈላጊ ነው። የኋላ መብራት ሁሉንም አጥርቶ ቢያሳይም (ለደርጎች ብቻ ነው ይህ ክብዶና አልሆን ብሎ ያለው!) ያኔ የነበረው ሁኔታና አማራጭ ምን ነበር ብሎ መገምገሙ ጠቃሚ ነው ። ታሪካችን ስንጽፍ ይህንንም በግምታችን እያስገባን ነው። ለምሳሌ የትጥቅ ትግላችንን በኤርትራ በኩል ገብተን በአሲምባ እንጀምር ያልንበት በሌሎች ቦታዎች በኩል (ባሌ፤ ጎንደር፡ ሊሳካልን ባለመቻሉ ነው ። በዚያ ከሚጀመር ቢቀር ይሻል ነበር ማለት ይቻላል --ግን ትግሉ መጀመር አለበት የሚለው ከታመነበት በሚቻለው መንገድ መጀመር አማራጭ አልነበረውም ። ዛሬም ቢሆን የአካባቢ ሀገሮች ሁኔታ ሲታይና በተለይም ከሃገር ውስጥ መጀመር ካልተቻለ የትጥቅ ትግሉ ከየት እንዴት የሚሉት ጥያቂዎች አንገብጋቢ ሆነው ይገኛሉ ። በሩስያ ተመክሮ የጥቅምት አብዮት አለጊዜው ነበር የመጣው ብለው የሚያዝኑ እንደነበሩት ሁሉ ኢሕአፓም ከመመስረቱ በፊት እንደ ቦልሺቪኮች (ከእነ ሊኒን ፓርቲ) በቅድሚያ ኢስክራ ዓይነት  ጋዜጣ አውጥቶ፤ በርዕዮት ተፋጭቶ ከዚያ በኋላ ነበር መመስረት የነበረበት የሚሉም ነበሩ ። ይህ ጥያቂ ከብተና በኋላ በርቲያ በሚባል ቦታ በተደረገ ስብሰባ ሲነሳ ጸጋዬ ደብተራው የሰጠው መልስ ትዝ ይለኛል-- *"ድርጅቱ ሲመሰረት ከሰንት አመት በኋላ በርቲያ በሚባል ቦታ አንድ አባል ተነስቶ ምስረታው ስህተት ነበር ይለናል ብለን ብንሰጋ ኖሮ በመሰረትንበት ጊዜ ባልመሰረትነው ነበር"* የሚል ነው ። ቢደረግ ኖሮ፤ ቢሆን ኖሮ የጊዜ ምቾትን --በሀገራችን መገኘት ያልተቻለውን-- ጠያቂ ናቸው ። የኋላ መብራት ስህተቱንም ድሉንም ቁልጭ አድርጎ ያሳያልና--ካለፈ ከተደረገ ከሆነ በኋላም ነውና- ያኔ አይበራም ። ምኒሊክ ይህን ቢያደርጉ ባያደርጉ ብሎ ዛሬ መቆጨት ከንቱ ነው --በተለይም ተቺዎቻቸውና አውጋዦቹ ዛሬ ባለንበት ዘመናዊ ተብዪ ጊዜ ማንነታቸውን በአሶሳ፤ በደኖና አርባጉጉ ፍጅት እየገለጹ ። ለነገሩ ወያኔ በራሱ ችግርና ቀውስ መጠበቅ እስኪወድቅ ሲቻል በደከምንበትም ሁኔታ ትግልን መቀጠል ግን ሀገር አድን ትግሉ ግዴታችሁ ነው የሚለን ነው ። ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም ተብሏል--ስህተት ደግሞ በገቢር ከተሰማራ ሁሉ የሚጠበቅ ነው ። ስህተተ ተፈርቶ፤ መስዋዕትነት ተሸሾ  ትግል የለም-- ባርነትና ውርደት ግን ከተሜዎቹ እንደሚሉት በሽበሽ ይሆናል ።

ኢትዮጵያ የአስርን እናት ጅብ በላት ሁኔታ ውስጥ ከገባች ዓመታት አለፉ። አዲስ ክስተት አይደለም ። የኢሕአፓንና የዚያን ጀግና ትውልድ ታሪክ የሚያደርገው የሀገርና የብዙሃኑን ኡኡታ ሰምተው በመታገላቸውና ትግሉም የሚጠይቀውን መስዋዕትነት መክፈላቸው፤ የትግሉ ነው ሕይወቴ ማለታቸው፤ ሞት አይፈሪ መሆናቸው ነው ። ይህ ከዛሬ ተጨባጭ ሁኔታ ሲወዳደር ልዩነቱ ሰማይና ምድር መሆኑ የሚካድ አይደለም ። ሙት ይዞ ይሞታል አልተባለም ያኔ--መሞት ለሌላው አርአያ ሆነ እንጂ፤ ትግሉን አስቀጠለ እንጂ፤ ክቡር መስዋዕትነት ሆነ እንጂ ። ደርግና ኢሕአፓ፤ ኢሕአፓና መኢሶን ፖለቲካዊ ልዩነት ነበራቸው--መሰረታዊ ልዩነት፡፡ ደርግ ባለው ጠባይና ይዞታ ይህን ልዩነት ወይም ኢሕአፓ በፖለቲካው መስክ ታግሎ ሊያቸንፈው ሲደርስ ህዝብ ካልፈለገኝማ ብሎ የሚለቅ አልነበረም፤ የመደብ ጠባዩም የሚፈቅድለት አልነበረምና ወደ አፈና ተሰማራ ። በዚህም የተባበሩት ታሪካዊ ስህተትን ፈጸሙ ። ጆን ስፒንሰር፤ ዶናልድ ሊቪን፤ ፒተር ሽዋብ፤ የወያኔ ጆን ያንግና ሊሎችም ስለ ኢሕአፓ ምስረታ ያልዘባረቁትም አልነበረም። ኢሕአፓ ግን በኢትዮጵያ ልጆች የትግል ፍላጎት የተመሰረተና ከምስረታው ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ሳይሰጥ የታገለ ድርጅት ነው። ይህ ችግር ቀፍቃፊ አቋሙ

ያስከተለበትን ችግር በታሪኩ ዘርዝሮ አስቀምጦ ማሳወቅ ቸል የማይለው ግዲታ ነው ። ኢሕ አፓ ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ቢያብርና ቢስማማ ኖሮ ዛሬ ባለስልጣን ሆኖ ሀገሪቷን አስተዳዳሪ በሆነ ነበር--- እንደ ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን እንደ ባዕድ ቅጥረኛ ማለት ነው ። ይህን ግን ድርጁት አልፈለገም ። አንዳንዶች ዘዴ አነሰው እንጂ ኢሕአፓ ተመሳስሎ ፤ ለስልጣን መብቃት ነበረበት ይላሉ ። ይህ እርምጃ ግን የሚጠይቀው ክፍያ ቀላል አልነበረም ። እነ ሱዳንን ተቀብሎ የአባይ ድልድይን ማፍረስ የሚጠይቅ ነበር ። ሻዕቢያ ቅኝ ግዛት ነን የሚለውን መቀበል የሚጠይቅ ነበር። ሌላም ሌላም ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የሚጎዱ ድርጊቶችን መቀበል የሚጠይቅ ነበር ። ይህን ኢሕአፓ መቀበል አልተቻለውም። አረብ ነን ማለት እንደ ወያኔ አልተዋጠለትም ። በመሆኑም እምቢታው ስልት ማጣት ሳይሆን ኢትዮጳያዊነትን ማስከበር ነበር ። ድርጅቱ የህገርና ሕዝብን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ ቢሆን ኖሮ፤ ሀገርንም በዚያው አሳልፎ ቢሸጥ ኖር ምናልባትም ወደ ቤተመንግስት ደርሶ ለሕዝብ ጿጋ ሳይሆን መርገም በሆነ ነበር ፡፡

ይቀጥላል